# 22ኛው የግንቦት 20 ድል በአል በጣሊያን ተከበረ

22ኛው የግንቦት 20 ድል በአል 400 የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ የጣሊያን ዜጐች በተገኙበት «የግንቦት 20 ሕዝባዊ ድሎችን በማስፋት የኢትዮጵያን ሕዳሴ እውን እናደርጋለን» በሚል መሪ ቃል ሰኔ 2 ቀን 2005 ዓ.ም. በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

በዚሁ ወቅት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊና በትግሉ ለተሰው ታጋዮች የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት ከተደረገ በኋላ በጣሊያን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ክቡር ሙሉጌታ አለምሰገድ በአሉን በተመለከተ ለታዳሚዎች ባሰሙት ንግግር አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 22 ዓመታት በሰላም፣ በልማትና በዲሞክራሲ ግንባታ ሂደቶች ሰፊና አኩሪ ሕዝባዊ ድሎችን ማስመዝገብ መቻሏንና በተለይ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ባለሁለት አሃዝ አገራዊ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ፤ የአምስት ዓመቱን የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ሙሉ በሙሉ በመተግበር አገራችንን ወደ መካከለኛ የገቢ ደረጃ ለማድረስ መላው ሕዝባችንና መንግሥት በቅንጅት ባደረጉት እንቅስቃሴ ባለፉት ሁለት ዓመታት በግብርና በአማካይ 6.95 በመቶ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ልማት በ2004 ዓ.ም. የ13.6 በመቶ በአጠቃላይ በ2003 እና 2004 የአገር ውስጥ ምርትን በአማካይ 10.3 በመቶ ማሳደግ መቻሉንና በሌሎች የማኅበራዊና የመሠረተ-ልማት ዘርፎች የተመዘገቡ ውጤቶችን በዝርዝር ገልፀዋል።

አምባሳደሩ በንግግራቸው በቅርቡ የፀደቀውን የዲያስፖራ ፖሊሲ ዓላማና ዋና ዋና ተግባራት ከገለፁ በኋላ በጣሊያን አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ በዲያስፖራ ፖሊሲው የተቀመጡትን ዋና ዋና ግቦች ለማሳካት አቅም ካለ በግል ወይም የሽርክና ኩባንያ በማቋቋም በአገር ቤት ኢንቨስት በማድረግ እንዲሁም የጣሊያን ባለሃብቶች በአገራችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ በመመልመል፣ በአሻሻጭ ወኪልነት በመሰማራትና ገዥዎችን በማፈላለግ የወጪ ምርቶቻችን ገበያ እንዲያገኙ በማድረግ፣ በአገራችን ተፈላጊ የሆኑት ገቢ ምርቶች በአነስተኛ ዋጋና ጥራታቸውን በጠበቀ መንገድ ወደ አገራችን እንዲገቡ በማድረግ፣ በቱር ኦፕሬተርነት በመሳተፍ የአገራችን የቱሪስት መስህቦች በማስተዋወቅና ቱሪስቶችን በመመልመል የቱሪስት ፍሰትን በማሳደግ፣ የአገራችንን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ የቁጠባ ሂሳብ በአገር ቤት ባንኮች በመክፈትና ወደ አገር ቤት የሚላከው ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ በማስተላለፍ፣ መንግሥት በቅርቡ ባወጣው የመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማኅበርና በ40/60 የቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ በመሆን፤ በጣሊያን ሃገር በሚኖርበት ጊዜ የአገሩ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት መብቱንና ጥቅሙን በተደራጀ መንገድ ለማስከበር የሚያስችለው የኮሚኒቲ ማኅበራት በመመስረት ተሳትፎውን ይበልጥ ማጠናከር እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል።

ከአምባሳደሩ ንግግር በመቀጠል በሮም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ምክር ቤት ተወካይ በእለቱ ለተገኙ ታዳሚዎች ም/ቤቱ ከተመሠረተ ጀምሮ ለግድቡ ግንባታ የገንዘብ ድጋፍ ለማሰባሰብ እያደረገ ላለው ጥረት በሮም ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እየተገኘ ላለው ድጋፍ አመስግኖ የግድቡ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

ከዚህም በመቀጠል በሮም በተቋቋመው የአማራ ልማት ማኅበር ኮሚቴ ተወካዮች ስለማኅበሩ ዓላማ ለታዳሚዎቹ ንግግር የተደረገ ሲሆን በሮም የሚገኙ የአማራ ክልል ተወላጆችና ሌሎች የልማት አጋሮች ከኮሚቴው ጐን በመሰለፍ ለክልሉ ልማት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አስተላልፈዋል።